**ፌርፋክስ ካውንቲ የተቀናጀ የማህበረሰብ ፈንድ አማካሪ ኮሚቴ**

# የህዝብ አስተያየት የመስማት ማስጠንቀቂያ

**ማክሠኞ ሚያዝያ 11/2023 በ6:30 pm**

**ይህ ሙሉ በሙሉ በቨርቿል የሚደረግ የህዝብ አስተያየት የሚሰማበት ፕሮግራም ነው። በዚህ ስብሰባ ላይ ለመሳተፍ ከዚህ በላይ ያለውን ኪውአር ኮድ ወይም ማስፈንጠሪያ በመጠቀም የኤምኤስ ቡድኖችን የሎግኢን መመሪያዎችን ይከተሉ:**
**https://bit.ly/CCFACApril2023**

**በድምጽ የተዘጋጀውን በነጻ ጥሪ የስልክ መስመር 571-429-5982 በመደወል እና ኮድ በማስገባት ማግኘት ይቻላል: 443 972 477#**

## ዓላማ

የፌርፋክስ ካውንቲ የተቀናጀ የማህበረሰብ ፈንድ አማካሪ ኮሚቴ (CCFAC) *የ2025-2026 የበጀት ዓመት የሁለት አመት ዑደት* የተቀናጀ የማኅበረሰብ ፈንድ ፑል አይነቶችን ረቂቅ (CCFP) የህዝብ አስተያየት እንዲሠጥበት ይፋ አድርጓል። CCFP ማለት በማህበረሰብ ተኮር ድርጅቶች ለሚሠጡ ብቁ ለሆኑ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች የፌርፋክስ ካውንቲ ውል የሚሠጥበት ተወዳዳሪ ሂደት ነው። በዚህ ተግባራዊ በሚደረግ የስራ ዕቅድ ላይ የሚቀርቡ አስተያየቶች በጽሁፍ ወይም ማክሠኞ ሚያዝያ 11/2023 በ6:30 p.m። በሚሠማው በCCFAC የህዝብ ችሎት ላይ ኦንላይን ሊቀርቡ ይችላሉ። CCFAC የህዝብ አስተያየቶችን ከተቀበለ በኋላ የ2025-2026 የበጀት ዓመትን የፈንድ አይነቶች ለተቆጣጣሪዎች ቦርድ በመፍትሔ ሃሳብነት ያቀርባል። ቦርዱ ማክሰኞ ሠኔ 27/2023 በሚያደርገው ስብሰባው CCFAC ያቀረበውን የውሳኔ ሀሳብ ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል ተብሎ የሚጠበቅ ሲሆን የ2025-2026 የበጀት ዓመት በሁለት ዓመት ዑደት በ2023 የበልግ ወቅት እንዲሠጥ የተጠየቀው የተቀናጀ የማኅበረሰብ ፈንድ ፑል (CCFP) የስራ እቅዶች መጠየቂያ (RFP) ውስጥ በሚካተቱት የፈንድ አይነቶች ላይ ይወስናል።

የፌርፋክስ ካውንቲ የተቀናጀ የማህበረሰብ ፈንድ አማካሪ ኮሚቴ (CCFAC) የሠብዓዊ አገልግሎት ድጋፍ የሚፈልጉትን ወይም እየተቀበሉ ያሉትን ጨምሮ ከሁሉም ነዋሪዎች እና ከአካባቢው ማህበረሰብ እና እምነት ላይ ከተመሠረቱ ድርጅቶች እና ለካውንቲው ነዋሪዎች ቀጥተኛ አገልግሎቶችን ከሚሠጡት ወይም ለዚሁ ማህበረሰብ ከሚከራከሩ የግል ተቋማት አስተያየቶችን መስማት ይፈልጋል።

ኦንላይን የህዝብ አስተያየት በሚሠማበት ጊዜ ተሳታፊዎች ስለፈንድ አይነቶች መረጃ ለመሠብሠብ በተዘጋጀው ውይይት ላይ ጥናት የማቅረብ እና የመሳተፍ እድል አላቸው።

## ተሳትፎ

**የህዝብ አስተያየት የሚሠማበት ፕሮግራም ላይ ለመገኘት:** ማክሰኞ ሚያዝያ 11/2023 ቀን 12 ሰአት ላይ የህዝብ አስተያየት በሚሠማበት ፕሮግራም ላይ በጥናት ወረቀት አቅራቢ ዝርዝር ውስጥ ለመካተት ከMichelle Thompson ጋር በኢሜይል michelle.thompson@fairfaxcounty.gov ወይም በስልክ ቁጥር 703-324-3218, TTY 711 ደውለው ይገናኙ።

**በጽሁፍ የተዘጋጁ አስተያየቶችን ለማቅረብ:** https://engage.fairfaxcounty.gov/ccfp2526 ላይ የ CCFP የህዝብ አስተያየት ጥናት ይሙሉወይም በፖስታ ለፌርፋክስ ካውንቲ የተጎራባቾች እና ማህበራዊ አገልግሎቶች መምሪያ ለ: Michelle Thompson፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ተቋማት አስተባባሪ፣ አድራሻ 12011 ገቨርንመንት ሴንተር ፓርክዌይ፣ 10ኛ የወለል ቁጥር #1002.1 ፌርፋክስ፣ ቨርጂንያ፣ 22035።

**የጥናት ወረቀቶች/በጽሁፍ የተዘጋጁ አስተያየቶች በሙሉ ሚያዝያ 11/2023 ከ12 pm በፊት መግባት አለባቸው**

## ለግምገማ ሊገኝ የሚችል ሠነድ

እባክዎ ይህን ድረ ገጽ ይጎብኙ https://www.fairfaxcounty.gov/procurement/sponsoredprograms/fundingpool ወይም ሠነዱን ኦንላይን ለመገምገም http://www.fairfaxcounty.gov/housing። በተጨማሪም ሰነዱ በፌርፋክስ ካውንቲ ገቨርንመንት ሴንተር፣ 12000 ገቨርንመንት ሴንተር ፓርክዌይ፣ ፌርፋክስ፣ ቨርጂንያ፣ 22035 በሎቢ ደረጃ በሚገኘው በዜጎች የመረጃ ዴስክ፣ በፌርፋክስ ካውንቲ ቤቶች እና ማኅበረሰብ ልማት መምሪያ፣ 3700 ፔንደር ድራይቭ፣ ፌርፋክስ፣ ቨርጂንያ፣ 22030 እና ጌሪ ሃይላንድ ገቨርንመንት ሴንተር፣ 8350 ሪችሞንድ ሀይዌይ፣ አሌክሳንድሪያ፣ ቨርጂንያ፣ 22309 ሊገመገም ይችላል። ከላይ የተገለጹት ቦታዎች በሙሉ አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ሠዎች ተደራሽ ናቸው። ሠነዱን በህትመት የሚፈልጉት ከሆነ፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር 703-324-3218 ደውለው ከMichelle Thompson ጋር ይነጋገሩ።

ፌርፋክስ ካውንቲ በሁሉም የካውንቲው ፕሮግራሞች፣ አገልግሎቶች እና ተግባራት ከአድልዎ የጸዳ አሰራር ለመከተል የሚተጋ ሲሆን በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት አግባብነት ያላቸውን አቅርቦቶች ይሰጣል። ልዩ አቅርቦቶችን ለመጠየቅ በስልክ ቁጥር 703-324-4600, TTY 711 ይደውሉ። አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ለማመቻቸት እባክዎ 48 ሠአት ይስጡ (ለተዘኑ የካፕሽን ጥያቄዎች 7 ቀናት)።

EQUAL HOUSING OPPORTUNITY